# 181st Semiannual General Conference
## Sunday Afternoon Session, October 2, 2011

ስለ ኢየሱስ ማስተማር

በሽማግሌ ዳለን ኤች ኦክስ

የአስራ ሁለቱ ሐዋሪያት ቡድን አባል

“ስለ ክርስቶስ ምን ይመስላችኋል?” (ማቴዎስ 22፥ 42) በእነዚህ ቃላት ኢየሱስ የዘመኑን ፈሪሳውያን አምታታ። በእነዚህ ቃላትም የኍለኛ ቀን ቅዱሳን ጓደኞቼን እና ሌሎች ክርስቲያኖችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ በእውነት ምን እንደሚያምኑ እና በእምነታችሁ ምክንያት ምን እያደረጉ እንዳሉ እጠይቃለሁ።

የምጠቅሳቸው ብዙዎቹ ቅዱሳት መጻፍችት የሚመጡት ከመፅሐፍ ቅዱስ ነው፣ ምክንያቱም ይህም ብዙዎቹ ክርስቲያኖች የሚያውቁት ነውና። የተለያዩ ክርስቲያኖች ስለትርጉሙ የምይጋቡበትን የመፅሐፍ ቅዱስ ጥቅሰቶች ትርጉምን ከሚያስተምረን ከአሁን ዘመን ቅዱሳት መጻህፍት ከሆነ ከመፅሐፈ ሞርሞን ነው የምገልጽበት የሚመጣው። የማንጋግረው የሚያምኑትን እና ሌሎችንም ነው። እራሳቸውን ክርስቲያን ብለው የሚጠሩት ኢየሱስን እንደ ታላቁ መምህር ያሞግሳሉ ነገር ግን መለኮታዊነቱን ማረጋገጥን ያስወግዳሉ። እነርሱን ለማነጋገር፣ የኢየሱስን ቃላት እጠቀማለሁ። እርሱ ስለእራሱ ማንነት እና ወደ ምድር ምን ለማድረግ እንደተላከ ያስተማረውን እንመልከት።

አንድያ ልጅ

ኢየሱስ አንድያ ልጅ እንደሆነ አስተምሯል። እንዲህም አለ፥
“በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።

“ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ፥ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ወደ ዓለም አልላከውምና።” (የሀንስ 3፥ 16--17)

እግዚአብሔር አብም ይህን አረጋገጠ። በቅዱስ አጋጣሚ መጨረሻም በመቀየሪያ ተራራ ላይ ከሰማይ እንዲህ አወጀ፥ “በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው፤ እርሱን ስሙት” (ማቴዎስ 17፥ 5)።

ኢየሱስ ደግሞም አመለካከቱ እንደ አባቱ አይነት እንደሆነም አስተምሯል። ለሐዋሪያቱ እንዲህ አለ፥

“እኔንስ ብታውቁኝ አባቴን ደግሞ ባወቃችሁ ነበር። ከአሁንም ጀምራችሁ ታውቁታላችሁ አይታችሁትማል አለው።

“ፊልጶስ። ጌታ ሆይ፥ አብን አሳየንና ይበቃናል አለው።

“ኢየሱስም አለው። አንተ ፊልጶስ፥ ይህን ያህል ዘመን ከእናንተ ጋር ስኖር አታውቀኝምን? እኔን ያየ አብን አይቶአል፤ እንዴትስ አንተ። አብን አሳየን ትላለህ?” (ዮሀንስ 14፥ 7 – 9)።

እንደዚህም ሐዋርያው ጳውሎስ ወልድን ገለጸ፣ "እርሱም የእግዚአብሔር አብ] መንጸባረቅ ሆነ።" (እብራውያን 1፥ 3፤ ደግሞም 2 ቆሮንቶስ 4፥ 4 ተመልከቱ)

## ፈጣሪ

ሐዋሪያው ዮሀንስ "ቃል፣" ብሎ ስለጠራው ኢየሱስ እንደጻፈው "በመጀመሪያው በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ። ሁሉ በእርሱ ሆነ፥ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም።" (ዮሀንስ 1፥ 2—3) በዚህም በአብ አላማ መሰረት ኢየሱስ ክርስቶስ የሁሉም ነገሮች ፈጣሪ ነበር።

## የእስራኤል ጌታ አምላክ

የፊልስጢ ህዝብን በሚያገለግልበት ጊዜ፣ ኢየሱስ ያህዌ፣ የእስራኤል ጌታ አምላክ እንደሆነ አወጀ (ዮሀንስ 8፥ 58 ተመልከቱ)። በኋላም፣ ከሞት እንደተነሳ ጌታ፣ በአሜሪካ ክፍለ አህጉር ያሉትን ህዝብ አገለገለ። እዚያም እንዲህ አወጀ፥

"እነሆ፣ እኔ ኢየሱስ ክርስቶስ ነኝ፣ ነቢያት ወደ ዓለም ይመጣል ብለው የመሰከሩልኝም።

"…እኔ የእስራኤል [ሐ]አምላክ፣ እናም የምድር ሁሉ አምላክ [ነኝ]…" (3 ኔፊ 11፥ 10፤ 14

## ለእኛ ምን አድርጎልናል

አበዙ አመት በፊት በካስማ ጉባኤ፣ ለብዙ አመታት ተሳታፊ ያልነበረች ሴት እንድትመለስ ጠይቃ ለምን መመለስ የሚገባባት ምንም ምክንያት ለማሰብ እንዳልቻለች ከነገረችኝ ሴት ጋር ተገናኘሁ። እርሷን ለማበረታታት እንዲህ አልኩኝ፣ "አዳኝ ስላደረገልን ነገሮች ሁሉ ስታስቢ፣ እርሱን ለማምለክ እና ለማገልገል ወደ ቤተክርስቲያን የምትመለሺበት ብዙ ምክንያቶች የሉሽምን?" እርሷም በመደነቅ እንዲህ መለሰች፥ "ለእኔ ምን አድርጎልኛል?" ለእኛ ምን እንዳደረገልን ለማይገባችሁ፣ ያን ጥያቄ በራሱ ቃላት እና በምስክሬ እመልሳለሁ።

## የአለም ህይወት

መፅሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ ያስተማረውን መዝግቧል፥ "ሌባው ሊሰርቅና ሊያርድ ሊያጠፋም እንጂ ስለ ሌላ አይመጣም፤ እኔ ሕይወት እንዲሆንላቸው እንዲበዛላቸውም መጣሁ"

(ዮሀንስ 10፥ 10)። በኋላም በአዲሱ አለም፣ እንዲህ አወጀ፣ “”የአለም ብርሀን እና ህይወት ነኝ” (3ኔፊ 11፡ 11)። የአለም ህይወት ነው ምክንያቱም እርሱ ፈጣሪያችን ነውና እናም በትንሳኤው በኩል እንደገና እንደምንኖር ማረጋገጫ አለንና። የሚሰጠን ህይወት የስጋ ህይወት ብቻ አይደለን። እንዳስተማረው፣ “እኔም የዘላለም ሕይወትን እሰጣቸዋለሁ፥ ለዘላለምም አይጠፉም፥ ከእጄም ማንም አይነጥቃቸውም።” (ዮሀንስ 10፥ 28፣ ደግሞም ዮሀንስ 17፥ 2 ተመልከቱ)

## የአለም ብርሀን

ኢየሱስ ደግሞም እንዳስተማረው፣ “እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ፤ የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም” (ዮሀንስ 8፥ 12) እንዲህም አውጇል፣ “እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ” (ዮሀንስ 14፥ 6)። እርሱም መንገድ ነው እናም እርሱም ብርሀን ነው ምክንያቱም ያስተማረው በስጋዊ ህይወት ጎዳናችንን ያበራል እናም ወደ አብ የምንመለስበትን መንገድ ያሳየናል።

## የአብን ፍላጎት ማሟላት

ሁልጊዜም፣ ኢየሱስ አብን ያከብራል እናም ይከተለዋል። እንደ ወጣትነቱም ለምድር ወላጆቹ እንዲህ ገልጿል፣ “በአባቴ ቤት እሆን ዘንድ እንዲገባኝ አላወቃችሁምን?” (ሉቃስ 2፥ 49) በኋላም እንዲህ አስተምሯል፣ “ፈቃዴን ለማድረግ አይደለም እንጂ የላከኝን ፈቃድ ለማድረግ ከሰማይ ወርጃለሁና” (ጆሀንስ 6፥ 38፣ ደግሞም ዮሀንስ 5፥ 19 ተመልከቱ)። አዳኝም እንዳስተማረው፣ “በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም” (ዮሀንስ 14፥ 6፣ ደግሞም ማቴዎስ 11፥ 27 ተመልከቱ)።

ወደ አብ የምንመለሰው የእርሱን ፈቃድ በማከናወን ነው።፡ ኢየሱስ እንዳስተምራረው፣ “በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ፥ ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም” (ማቴዎስ 7፥ 21)። እንዲህም ገልጿል፥

“በዚያ ቀን ብዙዎች። ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን፥ በስምህስ አጋንንትን አላወጣንምን፥ በስምህስ ብዙ ተአምራትን አላደረግንምን? ይሉኛል።

“የዚያን ጊዜም። ከቶ አላወቅኋችሁም፤ እናንተ ዓመፀኞች፥ ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ።” (ቁጥሮች 22--23)

ወደ ሰማይ መንግስት ማን ነው የሚገባው? ኢየሱስ እንዳስተማረው፣ የጌታን ስም በመጠቀም አስደናቂ ስራ ብቻ የሚሰሩት ሳይሆኑ፣ “በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ” (ቁጥር 21) ብቻ ናቸው።

## ታላቁ ምሳሌ

ኢየሱስ ይህን እንዴት እንደምናደርገው አሳይቶናል። በተደጋጋሚም እርሱን እንድንከተለው ጋብዞናል፥ “በጎቼ ድምፄን ይሰማሉ እኔም አውቃቸዋለሁ ይከተሉኝማል” (ዮሀንስ 10፥ 27)።

## የክህነት ስልጣን ሀይል

የክህነት ስልጣን ሀይል ለሐዋሪያቱና ለሌሎች ሰጥቷል (ማቴዎስ 10፥ 1 ተመልከቱ። ለታላቁ ሐዋርያ ጴጥሮስ እንዲህ አለው፣ “የመንግሥተ ሰማያትንም መከፈቻዎች እሰጥሃለሁ፤ በምድር የምታስረው ሁሉ በሰማያት የታሰረ ይሆናል፥ በምድርም የምትፈታው ሁሉ በሰማያት የተፈታ ይሆናል” (ማቴዎስ 16፥ 19፣ ደግሞም ማቴዎስ 18፥ 18 ተመልከቱ)።

ሉቃስም “ጌታ ሌሎቹን ሰብዓ ሾመ፥ ሁለት ሁለትም አድርጎ እርሱ ሊሄድበት ወዳለው ከተማና ስፍራ ሁሉ በፊቱ ላካቸው” (ሉቃስ 10፥ 1) ብሎ ጽፏል። በኋላም እነዚህ ሰባዎች በደስታ ለኢየሱስ “አጋንንት ስንኳ በስምህ ተገዝተውልናል አሉት” (ሉቃስ 10፥ 17)። ለዚህ የክህነት ስልጣን ሀይል ምስክር ነኝ።

## በመንፈስ ቅዱስ መመራት

በምድር አገልግሎቱ መጨረሻ ላይ፣ ኢየሱስ ሐዋሪያቱን እንዲህ አስተማረ፣ “አብ በስሜ የሚልከውግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል እኔም የነገርኋችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል” (ዮሀንስ 14፥ 26) እናም “ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል” (ዮሀንስ 16፥ 13)።

## በትእዛዛቱ መመራት

በትእዛዛቱም ይመራናል። በዚህም ኔፋውያንን በመካከላቸው ስለትምህርቱ በተመለከተ ጸብ እንዳይኖር አዘዛቸው፣ እንዲህም አለ፥

“እውነት፣ እውነት እላችኋለሁ፣ የፀብ መንፈስ ያለበት፣ የፀብ አባት ከሆነ እናም የሰዎችን ልብ እርስ በርስ እንዲጣሉ በቁጣ ከሚያነሳሳው ከዲያብሎስ እንጂ፤ ከእኔ አይደለም።

“እነሆ፣ ሰዎችን አንዳቸውን ከሌላኛው ልባቸውን ለቁጣ የሚያነሳሳ ይህ የእኔ ትምህርት አይደለም፤ ነገር ግን እንደነዚህ ያሉ ነገሮች እንዲወገዱ ማድረግ ይህ የእኔ ትምህርት ነው።” (3 ኔፊ 11፥ 29--30)

## የዘለአለም ህይወት ማተኮሪያ

በአለም ነገሮች ላይ ሳይሆን በእርሱ ላይ እንድናተኩር ጠይቆናል። በህይወት እንጀራ ስብከቱ ኢየሱስ በስጋዊና በዘለአለማዊ ምግብ መካከል ስላለው ልዩነት ገልጿል። “ለሚጠፋ መብል አትሥሩ፤ ነገር ግን ለዘላለም ሕይወት ለሚኖር መብል የሰው ልጅ ለሚሰጣችሁ ሥሩ” (ዮሀንስ 6፥ 27) አለ። እርሱ የህይወት እንጀራ፣ የዘለአለም ምግብ መንጭ እንደሆነ አዳኝ አስተምሯል። ኢየሱስ አለም ስለሚያቀርበው ስጋዊ ምግብ ሲናገር፣ በእዚህ እንጀራ የተመኩት አሁን እንደሞቱ አስተምሯል (ዮሀንስ 6፥ 49 – 50 ተመልከቱ) ከዚህ ጋር ሲመዛዘን፣ እርሱ የሚያቀርበው ምግብ “ከሰማይ የሚወርደው ህያው እንጀራ” ነበር፣ እናም ኢየሱስ እንዳስተማረው፣ “ሰው ከዚህ እንጀራ ቢበላ ለዘላለም ይኖራል” (ዮሀንስ 6፥ 51)።

አንዳንዱ ደቀ መዛሙርቱ ይህ ይህ የሚያስጨንቅ ንግግር ነው” አሉ (ቁጥር 60) እናም ከእዚያም ጊዜ ጀምሮ ተከታዮቹ “ወደ ኋላ ተመለሱ፤ ወደ ፊትም ከእርሱ ጋር አልሄዱም” (ቁጥር 66)። “መጀመሪያ የእግዚአብሔርን መንግስት ፈልጉ” (ማቴዎስ 6፥ 33) ብሎ ያስተማረውን አልተቀበሉም ነበር። አሁንም ክርስቲያን ነን የሚሉት አንዳንዶችም በአለም ነገሮች ላይ፣ እንዲሁም በምድር ላይ ህይወትን የሚደግፍ ነገር ግን ለዘለአለም ህይወት ምንም ምግብ ለማይሰጥ፣ ትኩረት አላቸው። ለአንዳንዶች፣ “የሚያስጨንቅ ንግግሩ” ክርስቶስን የማይከተሉበት ምክንያት ነው።

## የኃጢያት ክፍያ

የአዳኛችን የስጋዊ አገልግሎቱ መጨረሻ ትንሳኤውና ለአለም ኃጢያቶች ክፍያ ያደረገው ነው። መጥምቁ ዮሀንስ “እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ” (ዮሀንስ 1፥ 29) ባለበት ጊዜ ስለዚህ ተንብዮ ነበር። በኋላም ኢየሱስ ይህን አስተምሯል፣ “የሰው ልጅ ሊያገለግል ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ [መጥቷል]” (ማቴዎስ 20፥ 28)። በመጨረሻው እራትም፣ ኢየሱስ የባረከው ወይን “ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው” (ማቴዎስ 26፥ 28) ብሎ ገልጿል።

ወደ ኔፋውያን በመምጣት፣ ከሞት የተነሳው ጌታ በጎኑ ያለውን ቁስል እና በእጆቹና በእግሮቹ ያሉትን የችንካሬን ምልክት እንዲዳስሱ ዘንድ ጋበዛቸው። ይህንንም ያደረገው “እኔ የእስራኤል [ሐ]አምላክ፣ እናም የምድር ሁሉ አምላክ መሆኔንና፣ [መ]ለዓለም ኃጥያቶችም መገደሌንም እንድታውቁ ዘንድ” (3ኔፊ 11፥ 14) ነው ብሎ ገልጿል። ታሪኩም ቀጠለ፣ ህዝቦቹም “በኢየሱስ እግር ስር ወደቁ፣ እናም አመለኩት” (ቁጥር 17)። ለዚህም፣ አለም በሙሉ በመጨረሻም ያመልኩታል።

ኢየሱስ ስለ ኃጢያት ክፍያው ውድ እውነቶችን በተጨማሪ አስተማረ። ያስተማረውን የሚያብራራው እናም ስለሚስዮኑ ከሁሉም የሚሻል መግለጫ የሚሰጠው መፅሐፈ ሞርሞን ያስተማረውን ይዘረዝራል፥

“አባቴም በመስቀል ሀእሰቀል ዘንድ ልኮኛል፤ …ሰዎችን ሁሉ ወደ ራሴ ለአመጣ ዘንድ፣ …

“…በመሉ በስራቸው ይፈረድባቸው ዘንድ

“እናም…ማንኛውም ንስሃ የገባና በስሜየ ተጠመቀ ይሞላል፤ እናም እስከመጨረሻው [ሐ]“ከፀናም እነሆ ዓለምን የምፈርድበት ቀን ስትመጣ በአብ ፊት ከበደል የነፃ አደርገዋለሁ።”

“እናም በመንግስተ ሰማይ ምንም የረከሰ ነገር ሊገባ አይቻለውም፤ ስለዚህ በእምነታቸው እናም ለኃጢአታቸው ሁሉ ንስሃ በመግባታቸውና እስከመጨረሻው ባላቸው ታማኝነት በደሜ ልብሳቸውን ካጠቡት በስተቀር በእረፍቱ የሚገባ ማንም የለም።” (3ነፊ 27፡ 14-16፣ 19)

ስለዚህም የኢየሱስ ክርስቶስ የኀጢያት ክፍያ በኃጢያት ምክንያት የሚመጣውን መንፈሳዊ ሞት ለማሸነፍ እና ቅዱ ቃል ኪዳናት በመግባትና በመጠበቅ የዘለዓለም ህይወት በረከቶች እንዲኖረን እድል ይሰጠናል።

ጥያቄ እና ምስክር

ኢየሱስ ይህን ጠይቋል፥ “ስለ ክርስቶስ ምን ይመስላችኋል?” (ማቴዎስ 22፥ 42) ሐዋርያው ጳውሎስ የቆሮንቶስ ህዝብን “በሃይማኖት ብትኖሩ ራሳችሁን መርምሩ፤ ራሳችሁን ፈትኑ” (2ቆሮንቶስ 13፥ 5) ብሎ ጠይቋቸዋል። ሁላችንም እነዚህን ጥያቄዎች ለእራሳችን መመለስ አለብን። ፍጹም ታማኝነታችሁ ለማን ነው? ሽማግሌ ማክስዌል እንደገለጹት ወደ ፅዮን መኖሪያ ቢሰሩም ሁለተኛን ቤት በባቢሎን ለመጠበቅ እንደሚጥሩ ክርስቲያኖች አይነት ነን?

መካከለኛ መሬት የለም። የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮች ነን። ዜጋነታችንም በቤተክርስቲያኑ እና በወንጌሉ ነው፣ እናም ባቢሎንን ለመጎብኘት ቪዛ ሊኖረን ወይም እንደ ባቢሎን ዜጋ መሆን አይገባምንም። ስሙን እናክብር፣ ትእዛዛቱን እናክብር፣ እናም “የዚህ አለምን ነገሮች አትፈልጉ፣ አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመገንባት እናም ጽድቁንም ለመመስረት ፈልጉ” (Matthew 6:33, footnote a; from Joseph Smith Translation, Matthew 6:38)።

ኢየሱስ ክርስቶስ አንድያ ልጅ እና የእግዚአብሔር ውድ ልጅ ነው። እርሱም ፈጣሪያችን ነው። የአለም ብርሀን ነው። ከኃጢያትና ከሞት የሚያድነን ነው። በምድር ካሉት እውቀቶች ሁሉ በላይ የሆነ ነው፣ እናም ይህን እኔ ለእራሴ እንዳወቅኩት፣ ለእራሳችሁ ለማወቅ ትችላላችሁ። ስለ አብና ወልድ የሚመሰክረውና ወደ እውነት የሚመራን መንፈስ ቅዱስ እነዚህን እውነቶች ገጾልኛል፣ እናም ለእናንተም ሊገልፅላችሁ ይችላል። መንገዱም ፍላጎትና ታዛዥነት ነው። ኢየሱስ እንዳስተማረው፣ “ለምኑ፥ ይሰጣችሁማል፤ ፈልጉ፥ ታገኙማላችሁ፤ መዝጊያን አንኳኩ፥ ይከፈትላችሁማል” (ማቴዎስ 7፥ 7)። እናም “ፈቃዱን ሊያደርግ የሚወድ ቢኖር፥ እርሱ ይህ ትምህርት ከእግዚአብሔር ቢሆን ወይም

እኔ ከራሴ የምናገር ብሆን ያውቃል”(ዮሀንስ 7፥ 17)። ስለእነዚህ ነገሮች እውነትነት የምመሰክረው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነው፣ አሜን ።